| | |
|---|---|
| ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ | ረጀብ 18/1441 ሂ. |
| አውቃፍ ሚኒስትር | ማርች 13/2020 ግ. |

**የሰማእት ግንዛቤና የሰምኣታት ደረጃዎች**

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{وَالشُّهَدَاءُ عِندَ رَبِّهِمْ لَهُمْ أَجْرُهُمْ وَنُورُهُمْ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (በጌታቸውም ዘንድ መስካሪዎቹ ናቸው፡፡ ለእነርሱ ምንዳቸው ብርሃናቸውም አልላቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

አላህ (ዐ.ወ.) ለሰማእትነት የመረጣቸውና በሱም የለያቸው አያሌ ባሮች አሉት፡፡ አላህ (ሱ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡፡

**{وَلِيَعْلَمَ اللَّهُ الَّذِينَ آمَنُوا وَيَتَّخِذَ مِنْكُمْ شُهَدَاءَ}**

ትርጉሙም (እንድትገሰጹና) አላህም እነዚያን ያመኑትን እንዲያውቅ (እንዲለይ) ከእናንተም ሰማዕታትን እንዲይዝ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡ የሰማእትነት ደረጃ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ በርካታ ፍትዎችን አዝሏል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድሁም የሱ መላእክት (ዐ.ሰ.) ለነሱ ገነት የተዘጋጀላቸው መሆኑን የመሰከሩላቸው፣ እነሱም ከጌታቸው ዘንድ እየተመገቡ ያሉ ሕያው በመሆናቸው፡፡ አላህ ያዘጋጀላቸውን ተድላ እንድሁም አላህ ቃል የገባላቸው ነገርሁሉ እውነተኛ መሆኑን በቅርብ ስለሚመለከቱ እንድሁም የመሳሰሉ ሌሎች በርካታ ክብር የሚጨምሩ ነገሮችን የተሰጡ በመሆናቸው የሰማእትነት ትርጉም እጅጉን በዝቶ እናገኘዋለን፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ላል፡

وَالَّذِينَ قُتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ فَلَنْ يُضِلَّ أَعْمَالَهُمْ * سَيَهْدِيهِمْ وَيُصْلِحُ بَالَهُمْ * وَيُدْخِلُهُمُ الْجَنَّةَ عَرَّفَهَا لَهُمْ . }

ትርጉሙም (እነዚያንም በአላህ መንገድ ላይ የተገደሉትን ሥራዎቻቸውን ፈጽሞ አያጠፋባቸውም፡፡ በእርግጥ ይመራቸዋል፡፡ ኹኔታቸውንም ሁሉ ያበጃል፡፡ ገነትንም ያገባቸዋል፡፡ ለእነርሱ አስታውቋታል፡፡) ማለት ነው፡፡

ለአላህ እዝነት መረጋገጥ አንድ ሰው ሕይወቱን ለሀገር ክብር አሳልፎ ከመስጠት የበለጠ ተስፋ ያለው ነገር የለም፡፡ ስለሀገር ሲከላከል በመውደቁም እጅግ ታላቅ የሆነውን የሰማእተነት ደረጃን ያገኛል፡፡ ይህም የማይከሰር ትርፋማ ንግድ መሆኑን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ሲል ገልጾአል፡

إِنَّ اللَّهَ اشْتَرَى مِنَ الْمُؤْمِنِينَ أَنفُسَهُمْ وَأَمْوَالَهُم بِأَنَّ لَهُمُ الْجَنَّةَ }

ትርጉሙም (አላህ ከምእምናን ነፍሶቻቸውንና ገንዘቦቻቸውን ገነት ለእነሱ ብቻ ያላቸው በመኾን ገዛቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ይህ ከአላህ ዘንድ ታላቅ ደረጃ ያለው የአላህ መንገድ ሰማእትነት በርካታ ከፍሎች አሉት፡፡ ከነሱም መካከል እጅጉን ታላቁ ሀገር በመከላከል ላይ እያለና የአላህን ውዴታ በመፈለግ ሰማእት ሆኖ መውደቅ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አላህ (ዐ.ወ.) ዘንድ ከሁለት ጠብታዎችና ከሁለት ምልክቶች የበለጠ ተወዳጅ ነገር የለም፡፡ በአላህ ፍራቻ የምትወርድ የእንባ ጠብታና በአላህ መንገድ የምትፈስ የደም ጠብታ ሲሆኑ ሁለት ምልክቶች የተባሉት ደግሞ በአላህ መንገድ የሚፈጠሩ (እንደ ቁስል ያሉ) ምልክቶችና ከአላህ ግዴታዎች አንዱን በማድረስ የሚከሰቱ (እንደ በውዱ ምክኒት አግር መሰንጠቅ ያሉ) ምልክቶች ናቸው፡፡)

በደረጃ ከዚህ ከተጠቀሰው ሰማእትነት የማይተናነሱ በርካታ የሰማእት ዓይነቶች አሉ፡፡ ከነሱም መካከል ለሀገር ደህንነት ወይም ጸጥታን ለማስከበር ወይም ቤተጸሎቶችን የሚጠብቅ ፖሊስ እንድሁም ሀገርን ለመጎብኘት የመጡ እንግዶችን ደህንነት ለማስከብር ቅርሶችን በመጠበቅ በተማኝነት ሥራውን ለማከናውን የሚዋደቅ ሰማእት የሚሉት ይካተታሉ፡፡ እነዚህን የመሰሉም የህዝብን ነብረት ለማስከበር በሚደረግ ጥበቃ መዋደቅም በአላህ መንገድ መዋደቅ ነው፡፡

እንድሁም ራሱን ወይም ሌላን ሰው፣ ክብሩን ወይም የሌላን ሰው ክብር፣ ንብረቱን ወይም የሌላን ሰው ንብረት ሲከላከል ህይወቱን ያጣም ሰማእት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ስለገንዘቡ ሲከላከል የሞተ ሰው ሰማእት ነው፡፡ ደሙን ለማስከበር የተገደለ እሱ ሰማእት ነው፡፡ ሰለሃይማኖቱ ሲከላከል የተገደለ ሰው እሱ ሰማእት ነው፡፡ ቤተሰቡን ሲከላከል የተገደለ ሰው እሱ ሰማእት ነው፡፡) እነዚህ ሁሉ ሰለሀገራቸው ክብርና ስለእምቅ ሀብቷ ሲከላከሉ ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ ናቸው፡፡ እንድሁም የእስልምና እምነት መዳፈሩን እርም ያደረገውንና እንዲጠበቅም ያዘዘውን ንብረትን፣ ሕይወትንና ክብርን ሲጠብቁ ሕይወታቸውን ያጡም ሰማእታት

ናቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በማንኛውም ሙስሊም ላይ የሙስሊም ደም፣ ግንዘብና ክብር መዳፈር የተከለከለ ነው፡፡)

ሰማእትነት አላህ ለመረጠው ባሪያው የሚቸረው ስጦታ በመሆኑ በትንሳኤ ቀን የሰማእት ደረጃ ከነብያትና ከአላህ መልክተኞች ደረጃ ቀጥሎ ያለው ደረጃ ነው፡፡ የሰማእተነት ፍሬዎች በረካታ ሲሆኑ በመጀመሪያ የሚጠቀሰው እነሱ የሞት ስቃይ የማያገኛቸው መሆኑ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሰማእት ከሞት ስቃይ እንዳችሁ ከ(ጉንዳን..) ቁንጠጣ እንደሚሰማው ያህል እንጂ ስቃይ አይሰማውም፡፡)

የሰማአትነት ሌላው ትሩፋት ደግሞ ከቀብር ስቃይና ፈተና ነፃ መሆናቸው ነው፡፡ ከእለታት አንድ ቀን አንድ ግለሰብ ለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ሲል ጠየቀ ‹ሙእሚኖች ከነሱ ሰማእት ሲቀር የቀበር ፈተና የሚደርስባቸው ለምንድን ነው? እሳቸው (የጎራዴዎች ነጸብራቅ በራሱ በላይ ሲያንጃብብ የደረሰበት ፈተና ይበቃዋል ስለሚባል ነው) በማለት መለሱለት፡፡

ሌላኛው የሰማእትነት መልካም ፍሬ ደግሞ የደግ ሥራቸው ምንዳ ለዘለአለም የማይቋረጥ መሆኑ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ማንኛውም ሰው ሥራው በመሞቱ ያከትማል፡፡ በአላህ መንገድ ዘብ ቁሞ የሞተ ሰው ሲቀር፡፡ እሱማ ስራው እስከእለተ ቂያማ ድረስ ይባዛለታል፡፡ የቀብርን ፈተናም አይፈራም፡፡) ሰማእት ሰፊ ምንዳና ታላቅ ስጦታ አለው፡፡ እሱ በመጀመሪያ ደም ጠብታው ከአላህ ዘንድ ምህረትን ያገኛል፡፡ ከዚያም በጀነት ውብ መኖሪያውን ያያል፡፡ ከቀብርም ስቃይ ይጠበቃል፡፡ ከታላቁ ድንጋጤም ይሰወራል፡፡

ሰማእት በትናሳኤ ቀን ከሱ የምስክ ጠረን የሚያውድ ሆኖ በክብር ይነሳል፡፡ ነብያችን (ሶ.ሊ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሕይወቴ በእጁ በሆነችው በአላህ እምላለሁ አንድ ሰው በአላህ መንገድ አይቆስልም -አላህ በሱ መንገድ የሚቆስልን ያውቃል- በትንሳኤ ቀን ቀለሙ የደም ቀለም ጠረኑ ደግሞ የምስክ ጠረን ሆኖ የሚነሳ ቢሆን እንጂ፡፡)

ይህን ቃሌን ተናገርኩኝ፡፡ ለኔና ለናንትም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁኝ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

የተከበሩ ሰማእታቶቻችን የመስዋእትነት፣ የወንድነት፣ የክብርና የሃይክ ተምሳሌት በመሆን በህዝብ አእምሮ ተቀርጸው ለዘላለም ይኖራሉ፡፡ የአላህ ፈቃድ ሆነና ብጤ የለላትን እውነተኛና ዘላለማዊ ሕይወትን ሰጣቸው፡፡) አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

وَلَا تَحْسَبَنَّ الَّذِينَ قُتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ أَمْوَاتًا بَلْ أَحْيَاءٌ عِنْدَ رَبِّهِمْ يُرْزَقُونَ * فَرِحِينَ بِمَا آتَاهُمُ اللَّهُ مِنْ فَضْلِهِ وَيَسْتَبْشِرُونَ بِالَّذِينَ لَمْ يَلْحَقُوا بِهِمْ مِنْ خَلْفِهِمْ أَلَّا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ * يَسْتَبْشِرُونَ بِنِعْمَةٍ مِنَ اللَّهِ وَفَضْلٍ وَأَنَّ اللَّهَ لَا يُضِيعُ أَجْرَ الْمُؤْمِنِينَ} ،

ትርጉሙም (እነዚያን በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸው: : በእርግጥ እነርሱ እጌታቸው ዘንድ ሕያዋን ናቸው፤ ይመገባሉ፡፡ አላህ ከችሮታው በሰጣቸው ነገር ተደሳቾች ሲኾኑ (ይመገባሉ)፡፡ በነዚያም ከኋላቸው ገና በእነርሱ ባልተከተሉት በእነርሱ ላይ ፍርሃት ባለመኖሩና እነርሱም የማያዝኑ በመኾናቸው ይደሰታሉ፡፡ ከአላህ በኾነ ጸጋና ልግስና አላህም የምእምናንን ምንዳ የማያጠፋ በመኾኑ ይደሰታሉ፡፡) ማለት ነው

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ መንፈሳቸው በአላህ ዙፋን የተንጠለጠለ ጧፍ በአላቸው አረንጓዴ አእዋፍ ሆድ ውስጥ ሆኗ በጀነት ውስጥ እንደፈለጉ ይንቀሳቀሳሉ ከዚያም በነዚያ ጧፎች ይሰፍራሉ፡፡ ጌታቸውም በሚመለከታቸው ጊዜ የምትፈልጉት ነገር አለን? ሲል ይጠይቃቸዋል፡፡ እነሱም ምን የምንፈልገው ነገር ይኖራል እኛ በጀነት ውስጥ እንደፈልግን እየተንቀሳቀስን አሉ፡፡ ሦስት ጊዜ ይህን ተግባር ፈጸመ፡፡ እነሱም ከመጠየቅ የማያመልጡ መሆኑን ሲገነዘቡ ጌታችን ሆይ! መንፈሳችንን ወደ አካላችን እንድትመልስልንና እንደገና በአንተ መንገድ እንዲንገደል እንፈልጋለን አሉ፡፡ የሚፈልጉት ነገር እንደሌለ ባየ ጊዜ አነሱ ባለበት እንዲዘልቁ ተተዉ፡፡

እዚህ ላይ ልንጠቁመው የምንፈልገው ነገር ቢኖር ማንኛውም ሰው ከልቡ ሰማእነትን ከአላህ ዘንድ ከለመነ አላህ (ሱ.ወ.) በእርግጥ የሚሰጠው መሆኑን ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከልቡ ሰማእትነትን ከአላህ ዘንድ የጠየቀ ሰው ከአልጋው ላይ ተኝቶ ቢሞትም እንኳ አላህ የሰማእታትን ደረጃ ይሰጠዋል፡፡) አንድ ሰው ሃይማኖቱን በማስከበር ሀገሩን በመጠበቅና እምቅ ህባቷን በመከላከል እየተጨነቅ በአለበት ወቅት ቢገደል ሰማእት ይሆናል፡፡ አላህ ለሰማእትነት የመረጠውና ከነብያት፣ ከጻድቃንና ከመልካሞቹም ጋር እንድኖር የተመረጠ ሰው ምንኛን ታድሏል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَمَنْ يُطِعِ اللَّهَ وَالرَّسُولَ فَأُولَئِكَ مَعَ الَّذِينَ أَنْعَمَ اللَّهُ عَلَيْهِمْ مِنَ النَّبِيِّينَ وَالصِّدِّيقِينَ وَالشُّهَدَاءِ وَالصَّالِحِينَ وَحَسُنَ أُولَئِكَ رَفِيقًا} .

ትርጉሙም (አላህንና መልክተኛውንም የሚታዘዝ ሰው እነዚያ ከእነዚያ አላህ በእነርሱ ላይ ከለገሳቸው ከነቢያት፣ ከጻድቃንም፣ ከሰማዕታትም፣ ከመልካሞቹ ጋር ይኾናሉ፡፡ የእነዚያም ጓደኝነት አማረ፡፡) ማለት ነው፡፡

ጌታችን ሆይ ለሰማእታቶቻችን ምህረት አድርግ አገራችንንም ከመጥፎ ነገር ጠብቅልን፡፡ አሜን